# “በዓለ መስቀል”

ከሥርጉተ ሥላሴ
መስከረም 2001 ዓ. ም.

የመስቀል በዓል ሃይማኖታዊ ቢሆንም መላ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለየ ሁኔታ ያከብረዋል። ልጆች፦ የመስቀል በዓል የደመራ በዓል ይባላል።መቼም አገራችን ኢትዮጵያ ልዩ የሆነች ወርቅ ሀገር ናት። የመስቀልን በዓል በአክብሮትና በብርሃን አጅባ የምታከብረው በአለም ከአሉ ሀገሮች ሁሉ እርሷ ብቻ ናት። ደስ አትልም ልጆች ሀገራችን ?

የመስቀል በዓል በእናት ሀገራችን በኢትዮጵያ በገጠርም ሆነ በከተማ በፍጹም ሁኔታ የሚከበር ብሔራዊ በዓል ነው። ስለ መስቀል ሳነሳ ስለ ጉራጌ ቤተሰብም ትንሽ ማውሳት እፈልጋለሁ።

ልጆች የጉራጌ ቤተሰብ ሥራን ባህሉ ያደረገ፣ ታታሪና ተወዳጅ ብሔረሰብ እንደሆነ ታውቃላችሁ? አዎ! ልጆች የመስቀል በዓል በጉራጌ ብሔረሰብ ፍጹም የሆነ ልዩ በዓላቸው ነው። ቤተሰቡም በጋራ ተሰብስቦ ቆጮ፣ ክትፎ፣ አይቤ በጎመን ፣ በቅቤ ጥሩ ሁኖ ተዘጋጅቶ በደስታ ፣ በፍቅር በጋራ ሲበላ፣ ሲጠጣ ይዋላል። ሲያስፈልግ ደግሞ ልጆች የቡላ ገንፎም አለ።

ሌላው ደግሞ ልጆች የገጠሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለየት ያለ ፍቅር ለመስቀል በዓል አለው። ለምሳሌ ጎንደርን

ላንሳላችሁ። በመላ ጎንደር ያሉ ገበሬዎች ሌሊቱን አይተኙም። በዚህ ሀገር በአዲስ ዓመት ርቸት እንደሚተኮሰው ከዚያ ደግሞ በጅራፍ ጩኸት አካባቢው ይደምቃል።ይህ ለገጠሩ ሕዝብ ልዩ ስሜት የሚፈጥር ባህላዊ ሂደት ነው።

ሌላ ደግሞ ልጆች በከተማና በገጠር የመስቀል በዋዜማው ደመራ ይደመራል። ንጋት ላይ ደመራው ይቀጣጠላል ሠፈርተኛው፣ ጎረቢታሞቹ ሁሉ ይሰበሰቡና ደመራውን እየዞሩና እየጨፈሩ ያጅቡታል። ከዚያ የጤፍ ዱቄት ተቦክቶ በዱባ ቅጠል ይጠቀለልና ከደመራው እሳት ውስጥ ይጨመራል። ርሚጦ ይባላል ልጆች። ሲበስል ይበላል። ወጣቶች ደግሞ ችቦ ያቀጣጥሉና ቤቱን ይለኩሱታል።የጎመን ምንቸት ውጣ፣ የገንፎ ምንቸት ግባ። እያሉ እያዜሙ ሌላ ሥርዓት ይፈጽማሉ።
ውይ ልጆች ረስቼው ደግሞ ሌላ ነገር አለላችሁ ከመንፈቀ ወይም ግማሽ ሌሊት በኋላ ወይም ማምሻው ላይ ወጣት ልጆች ተሰባስበው ፦

ሆያ ሆዬ ሆ፣
የኔ ጌታ ሆ፣
የሰጠኝ ሙክት፣
ከግንባሩ ላይ አለው ምልክት።

እያሉ ሠፈሩን ሁሉ ይዞራሉ። ስጦታ ከተሰጡ፦

አመት አውደ አመት ድገመን
እግዚአብሔር ይስጥልን።

በማለት ይመርቃሉ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና ሃይማኖት አማንያን ዘንድ ደግሞ በዋዜማው ምሽት ላይ መስቀል አደባባይ ላይ ደመራ ይደመራል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ የመንግሥት ተወካዮችና ሕዝቡ በተገኙበት ደመራው ይቀጣጠላል። ካህናትና መዘምራን በማኅሌት፤ በዝማሬና በወረብ እንዲሁም ሕዝቡ ደግሞ በሆታና በእልልታ በዓሉን በማጀብ በታላቅ ሥነ ሥርዓት ይከበራል። በቤተ ክርስቲያንም በዓሉ በማህሌት፣ በወረብና በቅዳሴ ይከበራል፡፡

ልጆች፦ እኛም ወርቆች፤ ባህላችንም ወርቅ ሀገራችንም ወርቅ ናት።

እንኳን ለብርሀነ መስቀሉ በዓል አደረሳችሁ!!!